# አሮጌው በር



# SERMON-1



በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን።

“ንዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር”

# አሮጌውን በር እናድስ!



በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም-አንድ አምላክ አሜን

## የትምህርቱ ዓላማ፤

፩ኛ-እግዚአብሔርን ማወቅ በራሱ ሕይወት ስለሆነ ለአምልኮ እንዲያግዘን፤

፪ኛ-የወልደ እግዚአብሔርን አምላክነቱን አዳኝነቱን ሰፋ አድርጎ ለማየት፤እና

፫ኛ-የቤተክርስቲያናችንን ዓለምን በወንጌል የመድረስ ራዕይ ለመደገፍ፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

## የትምህርቱ ዓላማዎች.....በሌላ አገላለጽ

† የትምህርቱ ዓላማዎች (በዋናነት)

- የቀደመውን የእግዚአብሔርን ጥልቅ ሃሳብ መለስ ብሎ በማየት፤ እግዚአብሔር እዉነተኛ ፥ ሴይጣን ዉሸተኛ ለማለት፥
- መዳናችንን በማስረገጥ ፤ የድነትን ጽንሰ ሃሳብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማስረዳት፤ ከተለመደዉ ዓይነትም ወጣ ብሎ የነገረ-ድነት ማጣቀሻ ጽሑፍ ለሚማርም ፥ ለሚያስተምርም ለማቅረብ፥
- ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በቃል ስለምንሰጠው ምስክርነት ግንዛቤያችንን ለማስፋት ፥ እና
- ከዘፍጥረት 1-3 ያሉትን ዋና ሃሳቦች አጉልቶ በማሳየት ፤ የዘፍጥረት መጀመሪያው አምላክ ፤ የተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስም ሁሉ አምላክ እንደሆነ በመግለፅ ላይ አነጣጥሯል።



† የትምህርቱ ዓላማዎች (ከግንዛቤ በማስገባት)፡

- ቀደም የተረዳነዉን እዉነት ለማጠናከር፥ የረሳነዉን ለማስታወስ፥ የተሳሳትነዉን ለማረም፥ ያላወቅነዉንም ለማሳወቅ ነው፤ ስለዚህ ሁላችንም ተማሪዎች ነን!
- ተናጋሪዉንና አነጋገሩን ሳይሆን የሚነገረዉን እዉነት ልክ እንደ ቤሪያ ክርስቲያኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ አኳያ በመመዘን ከተቻለ ሁሉንም ፥ ካልሆነ ከፊሉን መቀበል ብልህነት ሲሆን፥ ሁሉንም አለመቀበል ደግሞ የራስ መብት ነዉ።



## የትምህርቱ ይዘት.......

† የትምህርቱ ይዘት

- በሥላሴ አስተምሮ ላይ የቆመ ነው፥
- ጌታን እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔር የሚልና፤ አምላክነቱን የማዳን ስራዉንም በጥልቀት የሚያይ ነዉ፥
- በዚሁም፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል ወይም በርሱ ማመን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አንዱን ሃሳብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይመለከታል፥
- ዲኖሚኔሽኖችን አይደግፍም ፥ አይተችምም ፤ ይልቁንም የሐዋሪያትንና ሐዋሪያዊያን አበዉ ዶክትሪንን ያማከለ ነው፥
- ስለዚህም አከራካሪ ነጥቦችን ከሰዉ ልጅ ድነት ጋር ከተያያዙ ያለ አድሎ በድፍረት ያቀርባል።



† ትምህርቱ የቤተክርስቲያኗን መሰረታዊ አስተምሮ ፍሬም የጠበቀ ቢሆንም፤ ከሁሉ በመሻል ለማስተማር ሳይሆን፤ በመዘጋጀትም ይሁን በማቅረብ ለመማር የሚሰጥ በመሆኑ፤

✓ ይህች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ትምህርቱን የማረም መብት አላት።

✓ መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ የቃላት ግድፈቶችን በማረም ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ስለዚህ መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ፣ የጽሑፍ ግድፈቶችን እያረሙ፣ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።



ትምህርቱ ወጥ ሆኖ የተዘጋጀ ስለሆነም፤

በአንዱ ቦታ የተነሳ ጥያቄ በሌላ ቦታ ስለሚመለስ፤ የሚነሱብዎን ጥያቄዎች በመያዝ ሙሉዉን ትምህርት መከታተሉ ይመከራል።

መዳንዎን ለማረጋገጥም ይሁን ለሚድኑት ለመመስከር፤ ነገረ-ድነትን ሰዉ ቢጠይቅዎት ወይም ለሰዉ እንዴት እንደ እንደሚያብራሩ በአጭሩ አሁን ይጻፉና፤ ከትምህርቱ በኋላ የተረዱትን ወይም ያሰፉትን ወይም ያረሙትን አዲስ እዉነት ያነጻጽሩና ስላስተማርዎት እግዚአብሔርን ያመስግኑበት።



